## ዓለም አቀፍ ሕብረት ለፍትሕ - የኢትዮጵያ ጉዳይ የ"ኢኮሶክ" (ECOSOC) አባል ሆነ፤

ኪዳኔ ዓለማየሁ

እንደሚታወቀው፤ ECOSOC (Economic and Social Council)(ኢኮሶክ)(የኢኮኖሚና የማሕበራዊ መማከሪያ) ድርጅት ከተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ስድስት ዋና አካሎች አንዱ ነው። ስለ ኢኮኖሚና ማሕበራዊ ዓለም አቀፍ ጉዳዮች የሚመለከትና የሚያስተባብር ነው። ከሚያከናውናቸው ዋና ዋና ተግባሮች አንደኛው መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን እየመዘገበ ከኢኮሶክ ጋር ብቻ ሳይሆን ከቅርንጫፍ አካሎቹም ጋር የመገናኘት እንዲሁም በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የሰብአዊ መብት ሒደቶችና የድርጅቱ ጠቅላላ ጉባኤ ፕሬዚዳንት ዝግጅቶች የመሳተፍ እድል ያመቻቻል። ECOSOC's "consultative status provides NGO's with access to not only ECOSOC but also to its many subsidiary bodies, to the various human rights mechanisms of the United Nations, …… as well as special events organized by the President of the General Assembly."

ከተቋቋመ 7 ዓመት ያለፈው፤ ዓለም አቀፍ ሕብረት ለፍትሕ - የኢትዮጵያ ጉዳይ (Global Alliance for Justice – The Ethiopian Cause) (www.globalallianceforethiopia.org) የኢኮሶክ አባል ሆኖ መመዝገቡ እጅግ የሚያበረታታና የሚያስደስት ክስተት ነው። ምክንያቱም፤ ሕብረቱ ለተቋቋመበት ዓላማ ሁሉ በኢኮሶክ መመዝገቡ ጉዳዩ ዓለም አቀፍ ትኩረት እንዲያገኝ ሊያመቻችለት ስለሚረዳ ነው።

የሕብረቱ ዋና ዋና ዓላማዎች፤

1ኛ/ ፋሺሽት ኢጣልያ በኢትዮጵያ ላይ በፈጸመችው አሰቃቂ የጦር ወንጀል አንድ ሚሊዮን ኢትዮጵያውያን በመጨፍጨፋቸው፤ 525000 ቤቶችና 2000 ቤተ ክርስቲያኖች በመውደማቸው፤ ብዙ የኢትዮጵያ ንብረቶች ተዘርፈው አሁንም በኢጣልያንና በቫቲካን እጆች ስለሚገኙና ሌሎችም አስከፊ በደሎች በመከናወናቸው ሐገራችን ተገቢው ካሣ እንዲከፈላት፤

2ኛ/ በፋሺሽቱ ወንጀል፤ ቫቲካንም ተባባሪ ስለ ነበረች የኢትዮጵያን ሕዝብ ይቅርታ እንድትጠይቅ፤

3ኛ/ የተዘረፉት ንብረቶች ለኢትዮጵያ እንዲመለሱ፤

4ኛ/ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት በኢትዮጵያ ላይ የደረሰውን ወንጀል እንዲመዘግብ፤

5ኛ/ በቅርቡ፤ አፊሌ በምትባል የኢጣልያ ከተማ "የኢትዮጵያ ጨፍጫፊ" ለተሰኘው ለሮዶልፎ ግራዚያኒ የተሠራው መታሰቢያ እንዲወገድ ነው።

ዓላማዎቹን ለማሳካት ማሕበሩ ብዙ ተግባሮች አከናውኗል። ከነዚሁ ውስጥ፤

1ኛ/ ለኢጣልያ መንግሥት፤ ለቫቲካን፤ ለአውሮፓ አንድነት፤ ለአፍሪካ አንድነት ማሕበር፤ ለተባበሩት መንግሥታት ድርጅት፤ ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን፤ ወዘተ. ለኢትዮጵያ ፍትሕ በመጠየቅ አመልክቷል።

2ኛ/ ከኢትዮጵያ አርበኞች ማሕበር ጋር ለመተባበር ግንኙነቶቹን እያጠናከረ ነው።



የፋሺሽት ኢጣልያኖች ወንጀል በኢትዮጵያ!



የቫቲካን ቄስ የፋሺሽቱን ጦር ሲባርኩ!

3ኛ/ ቫቲካን የኢትዮጵያን ሕዝብ ይቅርታ እንድትጠይቅ የሚያመለክተው አቤቱታ ከላይ በተጠቀሰው በሕብረቱ ድረ-ገጽ ላይ እየተፈረመ ነው። እስካሁን ከ30 ሐገሮች በላይ የሚኖሩ 4200 ሰዎች አቤቱታውን ፈርመውታል።

4ኛ/ ሕብረቱ ያስተባበረው፤ 30 ከተሞች የሚገኙ ኢትዮጵያውያንና የኢትዮጵያ ወዳጆች፤ የየካቲት 12 ቀን የሰማእታት ቀን በየዓመቱ በሰላማዊ ሰልፍ፤ በጉባኤ እና/ወይም በጸሎት እንዲከበር አድርጓል።

ለወደፊትም ሕብረቱ በኢኮሶክና በሌሎች ተመሳሳይ ድርጅቶች እርዳታ በመጠቀም ለኢትዮጵያ የሚያስፈልገው ፍትሕ እንዲገኝ ጥረቱን ይቀጥላል።

የኢኮሶክ ምዝገባ ሰነድ ከዚህ በታች ይታያል።

# The Global Alliance for Justice - The Ethiopian Cause Inc.

## View Activities

Areas of expertise & Fields of activity:

**Economic and Social**:

- Human Rights
- International Law

**Peace and Development in Africa**:

- Peace in Africa

**Conflict Resolution in Africa**:

| | |
|---|---|
| | • Conflicts Resolution |
| Geographic scope: | International |
| Country / Geographical area of activity: | • Ethiopia<br>• Holy See<br>• Italy<br>• United States of America |
| Mission statement: | Pursuant to the International Genocide Convention and the Declaration of Human Rights, and on behalf of the victims and survivors of the Ethiopian Genocide of 1935-1941, the Global Alliance for Justice seeks an apology from the Vatican along with acknowledgement, equity, justice, and fair compensation for the Ethiopian people from all concerned, and for the UN to rightfully include the genocide of the Ethiopian people in the annals of its historical genocide records and archives, in order that this long-ignored and untold story may be preserved, for a future world humanity |
| Year established: | 2000 |
| Year of registration: | 2013 |
| Organizational structure: | Non Profit Corporation - State of Texas, USA |
| Number and type of members: | No members per corporate structure |
| Affiliation with NGO networks: | Ethiopian cultural and religious organizations |
| Funding structure: | • Donations and grants from domestic sources |